በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

Office of the Head of Government in
The Amhara National Regional State

ቁጥር አብክመ/ሀ 1234/ርጠ01/ሸ1/1
ቀን 8 /04/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን
ባህር ዳር፣

ጉዳዩ፡- **የመስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔን ስለማሳወቅ፣**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጥቅምት 01/2018 ዓ/ም ባካሄደው 6ኛ ዙር 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ስብሰባ የአብክመ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ማደራጃ ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

በዚህም መሰረት ደንቡ በዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ ሳይጠበቅ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን በመወሰኑ ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ ተስተካክሎ የመጨረሻ የህግ ቅርጽ የያዘውን የአብክመ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ማደራጃ ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፩/፪ሺ፲፰ ባለ 11 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አረጋ ከበደ ለጋስ
ርዕሰ መስተዳደር

ግልባጭ፣

- ለም/ር/መስተዳድሩ /ያለ አባሪ/
- ለጽ/ቤት ኃላፊ /ያለ አባሪ/
- ለካቢኔ/ጉ/ሴክሬታሪያት ዳይሬክቶሬት
  ርዕሰ መስ/ጽ/ቤት፣

## ደንብ ቁጥር ፪፻፴፩/፪ሺ፲፰ ዓ/ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኮንስትራክሽን ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባርን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

የክልሉን ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም በማጎልበት ዘላቂ የስራ ዕድል እንዲፈጥር እና ለክልሉ ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እንዲያድግ ለማድረግ ኮንስትራክሽን ዘርፉን የሚመራ ተቋም ማደራጀት አስፈላጊነቱ ስለታመነበት፤

የግንባታ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና ሌሎች በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የተሠማሩ አካላት በዘርፉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከዘመኑ ጋር አብሮ እንዲዘምን ለማስቻል ማነቆዎችን በመፍታት እንዲሁም የጥናት እና ምርምር ሥራዎች በማከናወን ተፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ መንግስታዊ ተቋም ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ኃብት፣ ገንዘብ እና እውቀት የሚንቀሳቀስበት እንዲሁም በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በተበታተነ መንገድ ሲመራ የነበረበትን ሁኔታ ቀይሮ ውጤታማነትን፣ተጠያቂነትን እና ግልፅነትን በሚያረጋግጥ አግባብ በተደራጀ መንገድ መምራት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት፤

በዲዛይን፣በጨረታ፣በኮንትራት ይዘት እና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ የቁጥጥር ሥርዓቱን ተግባራዊ በማድረግ በክልሉ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እና ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ ፯ እና በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ሥልጣን እና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፫፻/፪ሺ፲፰ ዓ.ም አንቀጽ ፹፩ ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

<u>**ክፍል አንድ**</u>

<u>**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**</u>

**<u>፩.አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኮንስትራክሽን ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ፪፻፴፩/፪ሺ፲፰ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**<u>፪.ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "**ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ**" ማለት የተለያዩ ተፈጥሯዊ ወይም የተፈበረኩ ግብዓቶች እና ሌሎች ሀብቶችን በመጠቀም ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ወደ ሆኑ የግንባታ ውጤቶች የሚለውጥ እና ተጨማሪ እሴት የሚፈጥር የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፤

፪/ **"የኮንስትራክሽን ሥራዎች"** ማለት ከመሬት በላይ እና በታች የሚከናወኑ የምህንድስና ፊዚካል መሠረተ ልማትን ጨምሮ በቋሚ ንብረቶች፣በአገልግሎቶችና በመሣሪያዎች የሚታገዙ የጉልበት ሥራዎች ጥምር ሆኖ በህንፃ ሥራዎች፣ በመሠረተ ልማት ሥራዎች፣ በማሕበራዊ አገልግሎት ተቋማት ሥራዎች፣ በሪክላሚሽን ሥራዎች፣በወደብ እና በሌሎች የሲቪል ግንባታ ሥራዎችን እንደ አዲስ የማልማት፣ የማስፋፋት፣ የመገጣጠም፣ የመጠገን፣ የማሻሻል፣ የማወላለቅ ወይም የማፈራረስ ተግባር ነው፣

፫/ **"የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት"** ማለት በመንግስት፣በግሉ ዘርፍ ወይም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ጥምረት የሚከናወኑ ማናቸውም የኮንስትራክሽን ምህንድስና ጥናት፣ዕቅድ፣ዲዛይን፣ ግዥ፣ማማከር እና የኮንስትራክሽን ሥራዎች ያጠቃልላል፤

፬/ **"የስራ ተቋራጭ"** ማለት ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ እንዲሳተፍ የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው እና የንግድ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፣

፫/ **"አማካሪ ድርጅት"** ማለት ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በአማካሪነት እንዲሳተፍ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው እና የንግድ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው፤

፯/ **"ባለሙያ"** ማለት ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ እንዲሳተፍ የሙያ ምዝገባ ፍቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፯/ **"ደረጃ"** ማለት ለጋራና ተደጋጋሚ ጥቅም መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፣ ሕጎች እና ተዛማጅ ሂደቶችን ላሟላ ባለሙያ ድርጅት፣ ማሽነሪ የጥራት መፈተሻ ላብራቶሪዎች እና ሌሎች ደረጃ ለሚሰጣቸው አካላት ስልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤

፰/ **"ስታንዳርድ"** ማለት በኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች ስራ ላይ እንዲውል በሀገራችን የተዘጋጀ እና ሀገራችን የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ቴክኒክ ሰነዶች ናቸው፤

፱/ **"ጥራት"** ማለት በቀጥታ የተገለፀን እና በተዘዋዋሪ መንገድ የተቀመጠን ፍላጎት የማሟላት ችሎታውን የሚገልፅ የኮንስትራክሽን ሥራ ግብዓት፣ውጤት ወይም አገልግሎት አጠቃላይ ባህርይ ነው፤

፲/ **"ቁጥጥር"** ማለት የኮንስትራክሽን ስራዎች እና አገልግሎቶች በተቀመጡ ሕጎች፣ኮዶች፣ ስታንዳርዶች እና ደረጃዎች መሠረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ ነው፤

፲፩/ **"የአሰራር ሥርዓት"** ማለት ባለስልጣኑ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማስፈፀም የሚውሉ ኮዶች፣ስታንዳርዶች፣ደረጃዎችና ማንዋሎች ስለሚዘጋጅበት፣ስለሚመሩበት እንዲሁም ወደ ተግባር የሚቀየሩበትን ሂደት የሚያሳይ ዘዴ ነው፤

፲፪/ **"መሠረተ ልማት"** ማለት ከመሬት በላይ ወይም በታች ያለ የሕንፃ፣ የመንገድ፣ የድልድይ፣የባቡር ሀዲድ፣የአውሮፕላን ማረፊያ፣የመናኸሪያ፣የኢነርጂ፣የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የመስኖ፣የውሃ፣የፍሳሽ ማስወገጃ እና ሌሎች ግንባታዎችን ይጨምራል፤

፲፫/ **"ቀመር"** ማለት ለኮንስትራክሽን ሥራዎች የዋጋ ግምት ትመና የሚመራበት አሰራር ዘዴ ነው፤

፲፩/ **"ሞዴል ዋጋ"** ቀድሞ የተገነቡትን እና አዳዲስ እየተገነቡ ያሉትን ግንባታዎች ከተለያዩ ከተሰሩበት የጊዜ፣ የግብዓት፣የሳይትና አካባቢ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ ዋጋዎችን በመሰብሰብ፣በማቀናጀትና በማስላት ለቀጣይ የግንባታ ግምት ሥራ የሚያገለግል የግንባታ መነሻ ዋጋ ነው፤

፲፪/ **"የአደጋ አጋጣሚዎች"** ማለት በኮንስትራክሽን ሥራዎች ሂደት ውስጥ እና አገልግሎት እየሰጡ ባሉ ግንባታዎች ላይ የሚደርስና በሰው፣በአካባቢ እና በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችል የጉዳት አጋጣሚ ነው፤

፲፫/ **"ባለሥልጣን"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ነው፤

፲፬/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭/ በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ያገለግላል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለኮንስትራክሽን ባለስልጣን አለማ፤አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባር</u>

### <u>፫.ተጠሪነት</u>

የኮንስትራክሽን ባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

### <u>፬.ዓላማ</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ፣ስታንዳርድ እና ደረጃን መሠረት ያደረገ እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እና ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር ማድረግ፤

፪/ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የዜጎችን እና አካባቢ ደህንነትንና ጤንነት ያረጋገጠ እንዲሆን በቅድመ ግንባታ፣በግንባታ እና በድህረ ግንባታ ወቅት ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቀጣይነት ያለው ክልላዊ እና ሀገራዊ ልማት ዕውን እንዲሆን ማስቻል፤

፫/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውል በተገባበት ዲዛይን፣ዋጋ፣ጥራት እና ጊዜ ተሰርተው እንዲጠናቀቁ በማድረግ የኃብት እና የጊዜ ብክነትን ማስቀረት፤

፬/ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ሃገራዊ ብሎም ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ያላቸው የግንባታ ተቋራጮች፣ባለሙያዎች እና አማካሪዎችን ማፍራት፡፡

## ፩.አድራሻ

የባለስልጣኑ አድራሻ በባህር ዳር ከተማ ይሆናል፡፡

## ፮.የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ፣ስታንዳርድ እና ደረጃን መሰረት በማድረግ የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ፣ስታንዳርድ እና ደረጃ ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፤

፪/ በሀገር ደረጃ የወጡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጆች፣ደንቦች፣ኮዶች፣ስታንዳርዶች፣ ደረጃዎች እና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መተግበራቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፤

፫/ በክልሉ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እና ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኢንዲፈጠር በዲዛይን፣በጨረታ፣በኮንትራት ይዘት እና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፤

፬/ በክልሉ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውንም የመንግሥት እና የግል የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ይመዘግባል፣ይቆጣጠራል፤

፭/ ለመሠረተ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሥራዎች ግንባታዎች ሞዴል ስፔሲፊኬሽን፣ የልኬት ሥርዓት እና ማኑዋል ያዘጋጃል፣ይከታተላል፣ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፤

፯/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውል በተገባበት ዲዛይን፣ዋጋ፣ጥራት እና ጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

፰/ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አሠራር ይዘረጋል፣አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፱/ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነት እና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤

፲/ በኮንስትራክሽን ሥራ እና ግንባታ አደጋ ሲፈጠር ምክንያቱን እና የጉዳት መጠኑን ያጣራል፣ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፣የሕግ ተጠያቂነት እንዲኖር ይሰራል፤

፲፩/ የግንባታ ሞዴል ዋጋዎችን እና የግምት መስሪያ ቀመሮችን ያዘጋጃል፣በዚሁ መሰረት የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለ መዘጋጀታቸው ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፤

፲፪/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ እና በከተማ ፕላን ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን ይመዘግባል፣ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ይሰርዛል፣ይቆጣጠራል፣ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና እንዲካሄድ ያደርጋል፤

፲፫/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ሥራ ተቋራጮች፣አማካሪዎች፣በዘርፉ ለሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶች እና በከተማ ፕላን ስራ ለሚሰማሩ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ያግዳል፣ይሰርዛል፣ይቆጣጠራል፤

፲፬/ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቁጥጥር የሚያገለግል መረጃ ይሰበስባል፣የመረጃ ቋት ያቋቁማል፣ወቅታዊ እና ተደራሽ ያደርጋል፤

፲፭/ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ደረጃ ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤

፲፮/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ከውጭ የሚገቡ የግንባታ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ መተካት የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤

፲፮/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በመንግሥት ኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚፈጠሩ የውል አለመግባባቶች አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ በመጠቀም በወቅቱ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፯/ የመንግሥት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አፈፃፀም ከጊዜ፣ከጥራት እና ወጭ አንፃር ክንውኑን ኦዲት ያደርጋል፣በሚገኙ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፰/ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማዘመን እና ማነቆዎቹን ለመፍታት የሚያስችሉ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ይሰራል፤

፲፱/ በክልሉ ውስጥ በኮንስትራክሽን ሥራዎች የግብዓት ጥራት ፍተሻ ስራ የተሰማሩ ላቦራቶሪዎችን ይከታተላል፣ይደግፋል፣ይቆጣጠራል፣በግኝቱም መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣እንደክፍተቱ መጠን በሕግ እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

፳/ በክልሉ መንግሥት በጀት እና በግሉ ዘርፍ ለሚገነቡ ማንኛውም ግንባታዎች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችን መርምሮ ያፀድቃል፣የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ከፍትህ ቢሮ ጋር በመሆን የመንግሥት የግንባታ ሥራ ውሎች በአግባቡ መዘጋጀታቸውን ክትትልና እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፳፩/ በክልሉ ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አቅም እንዲያድግ ተፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣የግንባታ ቴክኖሎጅዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፤

፳፪/ በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን የኮንስትራክሽን ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጅዎችን ይነድፋል፣ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፳፫/ የዲዛይን ለውጥን እና ተያያዥ ምክንያቶችን ተከትሎ የሚፈጠር ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች እና ተጨማሪ ዋጋ ሲያጋጥም የሚቀርብለትን ጥያቄ አጣርቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ሲፈቀድለትም በሕጉ መሰረት ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፳፬/ በሚመለከተዉ ተቋም ሲጠየቅ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶችን ለማካሄድ የሚዘጋጁ ቴክኒካል መመዘኛ ሰነዶችን፣ዲዛይኖችን እና የስራ ዝርዝሮችን ግምገማ ያካሂዳል፣ ያረጋግጣል፤

፳፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፳፬ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በየደረጃዉ በሚገኝ ከፍተኛ የመንግሥት የበላይ አመራር አስቀድሞ በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት መንግሥት የሚያካሂዳቸውን ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው ከፍተኛ የግንባታ ፕሮጀክቶች የጨረታ ሁኔታ ግምገማ ያካሂዳል፣በሴክተሮች የተካሄዱትን የከፍተኛ ፕሮጀክቶች የጨረታ ሁኔታ በማስቀረብ ይመረምራል፣ያረጋግጣል፣ያፀድቃል፤

፳፮/ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች እና የሰው ሐይል ወቅታዊ ዋጋ አጥንቶ በማቀናጀት ሴክተሮች እንዲያውቁት እና ስራ ላይ እንዲያውሉት ያደርጋል፤

፳፯/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ የህብረተሠቡ ተሣትፎ እንዲረጋገጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

፳፰/ የህንፃ ሹም ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣ይመራል፣ይቆጣጠራል፤

፳፱/ የክልሉ የግንባታ ተቋራጮች፣አማካሪዎች፣ባለሙያዎች እና ሌሎች በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የተሠማሩ አካላት በዘርፉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ተግባራዊ ያደርጋል፣ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፴/ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ እና የግንባታ መሣሪያዎች አቅርቦት ፈቃድ ይሰጣል፣ያድሳል፣ ጉድለት ካለ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፴፩/ የኮንስትራክሽን ዘርፉ በክልሉ ጥቅል ምርት ውስጥ የሚኖረው ድርሻ እንዲያድግ እና ለክልሉ ዕድገት እና ልማት የሚጠበቅበትን ሚና መወጣት እንዲችል ለማድረግ ስልቶችን ይቀይሳል፣በልዩ ትኩረት ይሰራል፣ይደግፋል፤

፴፪/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የኮንስትራክሽን እቃዎች ግዥ በጥራት እንዲፈፀም የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል።

## ፯.ተቋማዊ አደረጃጀት

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣

፪/ አንድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫/ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣን እና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ሲሆን የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፮ ሥር ለባለስልጣኑ የተሰጡትን ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይመራል፣ያስተዳድራል፤ በስራ ላይ ያውላል፡፡
፪ /በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ-

ሀ) በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የባለስልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፤

ለ) የባለስልጣኑን የሥራ ፕሮግራም፣ዓመታዊ እና ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል፣ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) የባለስልጣኑን የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

መ) ለባለስልጣኑ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ሠ) ባለስልጣኑን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤

ረ) የባለስልጣኑን የሥራ አፈፃፀም እና የሂሳብ ሪፖርቶች እያዘጋጀ ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል፤

ሰ) በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪/ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑን ስራ ለማሳለጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሥልጣን እና ተግባሩ በከፊል ለባለስልጣኑ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፱. የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣን እና ተግባራት

የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖራቸዋል፦

፩/ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ የባለስልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣በማደራጀት፣በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክተው ይሰራሉ፤

፬/ የስራው ውስብስብነት ሁኔታ እየታየ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚኖሩ ከሆነ ዋና ዳይሬክተሩ በተለየ የጽህፍ ውክልና የሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር እርሱን ተክቶ ባለስልጣኑን የሚመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይሆናል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ሹመቱ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠ ከሆነ ከተሿሚዎች መካከል ሴት ካለች ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ እና ፭ በተገለፀው መሠረት መለየት ካልተቻለ በአጠቃላይ የበለጠ የስራ ልምድ ያለው የሚመራ ይሆናል።

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲.ስለበጀት

የባለስልጣኑ የበጀት ምንጭ በመንግስት ከሚመደብለት በጀት ይሆናል።

### ፲፩. ስለሂሳብ መዛግብት እና ኦዲት

፩/ ባለስልጣኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤

፪/የባለስልጣኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውስጥ ኦዲተር፣በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ፲፪.ተፈፃነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፲፫.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ባለስልጣኑ በዚህ ደንብ የተሰጡትን ተግባራት እና ኃላፊነቶች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ረቂቅ መመሪያዎች አርቅቆ ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል፤በርዕሰ መስተዳድሩ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ፲፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት ከጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፰ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባሕር ዳር**

**ጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ/ም**

**አረጋ ከበደ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**